November 3, 2010

ለ፦ የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ

ጉዳዩ፦ በ28ኛው ዓመታዊ በዓል ላይ ስለሚጋበዙ የክብር እንግዳ

የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ በሚመጣው ዓመት በሚያካሒደው በ28ኛው ዓመታዊው በዓል ላይ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በክብር እንግድነት ለመጋበዝ በቀረበው ኃሳብ ላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሰነዘሩትን አስተያየቶች በአንክሮ በመከታተል ላይ ነን።

እኛ በአትላንታ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮ-አሜሪካውያን ይህንን ጉዳይ የምንከታተለው በሌሎች አካባቢዎች እንደሚገኙ ወገኖቻችን ሳይሆን፣ የተለየ ትኩረት በመስጠት ነው።

ለዚህም ቀዳሚ ምክንያት ለ28ኛ ጊዜ የሚካሔደውና፣ መላውን ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ የሚያሰባስበው ይህ ታላቅ በዓል የሚደረገው በከተማችን በአትላንታ በመሆኑና፣ ይህም በዓል ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ባማረ፣ በደመቀና፣ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሔድ ካለን ጽኑ ፍላጎት በመነሳት ነው።

የፌዴሬሽኑ ከፍተኛ አካል (ቦርድ) በ October 17 ቀን 2010 ዓ.ም የወ/ት ብርቱካንን ጉዳይ አንስቶ በተወያየበት ጊዜም የአትላንታ የስፖርት ቡድን ተወካይ አዎንታዊ ድምጹን መስጠቱ በአትላንታ የሚኖሩ በብዙ ሺህ ይሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ስሜትና ፍላጎት በትክክል ያንጸባረቀ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እንወዳለን።

ይሁን እንጂ፣ በፌዴሬሽኑ ድረ-ገጽ ላይ በተሰጠው መግለጫ፣ "Some senior board members implored and urged the Board to review the decision." በሚል መነሻነት ቦርዱ ቀደም ሲል በዲሞክራሲያዊ አግባብ ያሳለፈውን ውሳኔ ቀልብሶ፣ ወ/ት ብርቱካን እንዳይጋበዙ የወሰደው እርምጃ በእጅጉ አሳዝኖናል፣ አሰራሩም ተገቢ ነው ብለን ለማመን ተቸግረናል።

በመሰረቱ ቦርዱ በመጀመሪያ ጊዜ በድምፅ ብልጫ ያሳለፈው ውሳኔ የቦርዱ ውሳኔ ብቻ ሳይሆን፣ ከ27ቱ የቡድን ተወካዮች በስተጀርባ ያለው በመላ አሜሪካ የሚኖረው፣ ኢትዮጵያዊ ድምፅ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ይህንኑም እውነታ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ህዝቡ በተወካዮቹ አማካኝነት የሰጠው ድምፅ ሳይሻርበት ቦርዱ በቀድሞው ውሳኔ ፀንቶ ወደቀጣዩ ተግባር ቢገባ ኖሮ፣ ምንኛ አግባባዊ እርምጃ ተብሎ በተወሰደ ነበር።

ነገር ግን፣ በሺዎች የሚቆጠሩ በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተወካዮቻቸው አማካኝነት የሰጡት ድምጽ እንደመግለጫው አባባል፣ "<u>በጥቂት አንጋፋ የቦርድ አባላት</u> (Some senior board members)" (ሰረዝ የተጨመረ) ተሽሮ ህዝበ ውሳኔው መገልበጡን ስንሰማ ሁኔታውን በዝምታ ለማለፍ አልመረጥንም።

ስጋታችን፣ ለዓለም አቀፉ ለሳክሃሮቭ የሰብዓዊ መብት ሽልማት ለፍጻሜ ዕጩነት ከቀረቡትና ከአንድ እስከ ሦስት ከወጡት የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች መካከል አንዷ የሆኑት ወ/ት ብርቱካን፣ በክብር እንግድነት እንዳይገኙ መደረጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ ላለፉት 27 ዓመታት እያንዳንዱን ዜጋ በኢትዮጵያዊነቱ መስፈርት ብቻ በመመልከት በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን በማሰባሰብ የታወቀውና፣ ተደናቂነትን ያተረፈው ይህ ዓመታዊ የመገናኛ መድረክ፣ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ፣ ከፖለቲካና የሲቪክ ማኅበራ አልፎ ተርፎ፣ በኃይማኖት ድርጅቶችም ጭምር የተከሰተው የመከፋፈል ወረርሽኝ ፌዴሬሽኑንም እንዳይገርፈው በማሰብ ነው።

ሁላችንም እንደምንገምተው፣ ይህ ፌዴሬሽን ዛሬ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ የበለጠ ልቆና ተጠናክሮ ከመሔድ ይልቅ፣ ሲሆን ሲሆን ህልውናውን ጭራሹኑ እንዳያጣ ካልሆነ ደግሞ፣ የመከፋፈል ውሽንፍር መትቶት እንዲዳከም ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚሉ ፀረ-ህዝቦች እንዳሉ ከናንተ የተሰወረ ነው ብለን አናምንም።

በሌላ መልኩ ደግሞ፣ የህዝብ ፍላጎትን ያካተተ ውሳኔ በመውሰድ፣ ይህ በታላቅ ጉጉት የሚጠበቀው በዓል የሚገባውን ያህል ተመልካች እንዳያጣና ከዚያም ባሻገር አላስፈላጊ ወደሆነ መንገድ እንዳያመራ ከልብ የመነጨ ስጋት ስላደረብን ነው ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ የተገደድነው።

እንደሚታወሰው፣ ከዛሬ 5 ዓመታት በፊት 22ኛው የስፖርት በዓል የተካሔደው በዚሁ በአትላንታ ከተማችን ነበር። በፌዴሬሽኑ በ22 ዓመት ታሪክ ውስጥ ውድድሩ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ በዓለም ደረጃው ጥራቱ በተጠበቀና በታወቀው የBraves የቤት ውስጥ እስታዲየም እንዲካሔድ መደረጉና በወቅቱም በፌዴሬሽኑ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አግኝቶት የማያውቀው የተጣራ $153 ሺ.ህ ዶላር ትርፍ በአትላንታ በዓል ላይ መገኘቱን በዚህ አጋጣሚ ስናነሳ በኩራት መንፈስ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ያ ወቅት በአገራችን የህግ የበላይነትና የሁሉም ዜጎች እውነተኛ እኩልነት እንዲሰፍን የሚታገሉ ወገኖቻችን እህታችን ወ/ት ብርቱካንንም ጨምሮ፣ ለከፋ እስር የተዳረጉበት የጨለማ ዘመን ስለነበር፣ ይህንኑ ሁኔታ መነሻ በማድረግ፣ የሟቹ የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ የቅርብ ጓደኛና የትግል አጋር የሆኑት የ89 ዓመቱ (በዚያን ጊዜ 84 ዓመታቸው ነበር) እውቁ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች Reverend Joseph Lowery፣ በግንባር ቀደም የተሰለፉበትና ከ8 እስከ 10 ሺ.ህ የሚገመት ሕዝብ የተካፈለበት ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ የተደረገበት ወቅት እንደነበር ስናስታውስ አሁንም የልብ ኩራት እየተሰማን ነው።

ዛሬ ከ5 ዓመታት በኋላ፣ ታሪክ ራሱን በሌላ መልኩ ደገመና፣ በዓለም በሰብዓዊ መብት ተሟጋችነታችው የታወቁት ወ/ት ብርቱካን ለ2ኛ ጊዜ ብቻቸውን ተጥለው ከነበሩበት ወኅኒ ቤት ነጻ በወጡበት ጊዜ፣ የሰሜን አሜሪካ የስፖርት በዓል ደግሞ በአትላንታ እንዲካሔድ መወሰኑ የጊዜ አገጣጣሚውን በአድናቆት መመልከት ብቻ ሳይሆን፣ የአትላንታም ህዝብ ይህን የመሰለ የምሥራች ለማየት መብቃቱና ወ/ት ብርቱካንንም፣ በክብር እንግድነት ተቀብሎ፣ በአካል "እንኳን ለዚህ አበቃዎት!!" በማለት የደስታ ስሜቱን ለመግለጽ መቻሉ ዕድለኛ ነው ብለን እናምናለን።

ይህን ዕድል፣ የአትላንታም ሆነ ከሌሎች የአሜሪካ ግዛቶች የሚመጡ ኢትዮጵያውያን፣ ሊነፈጉ አይገባም። ሌላ ሳይሆን የኢትዮጵያዊነትና የሰብዓዊነት ስሜት መግለጫ ነውና!! የተለያዩ የውጭ አገር ድረጅቶችና የታወቁ ዓለም አቀፍ ተቋሞች እኚህን ታላቅ ሰብዓዊ ሴት፣ የሰው ልጆች እኩልነትና መሰረታዊ መብት እንዲከበር ሲሉ በከፈሉት መስዋዕትነት ተገቢውን ከበሬታና እውቅና በታሪክም ተገቢውን ስፍራ ሲሰጧቸው፣ እንዴት የኛው የራሳችን የሆነው የስፖርት ፌዴሬሽን ወ/ት ብርቱካንን "የፖለቲካ ሰው ናቸው" በሚል የተሳሳተ ትርጓሜ፣ የአንዲት ቀን እውቅና ይነፍጋቸዋል? እነዚህ ዓለም አቀፍ ተቋሞች እኮ ከበሬታውንና እውቅናውን ሲሰጧቸው ወ/ት ብርቱካን "የፖለቲካ ሰው ናቸው ብለው አልነበረም"።

ይልቁንም እነዚህ ተቋሞች፣ ወ/ት ብርቱካን ዓላማቸውም ሆነ ጥብቅና የቆሙት፣ አልፎ ተርፎም መከራና ስቃይ የተቀበሉት ለመላው ኢትዮጵያዊ ደህንነትና እኩልነት የቆሙ መሆናቸውን በማመናቸው ነበር።

በፌዴሬሽኑ ድረ-ገጽ መግቢያው ላይ፣ "Bringing Ethiopians together" የሚለው መፈክር በትክክል በተግባር ሊተረጎም የሚችለው ቦርዱ በ October 17 ቀን 2010 ዓ.ም በአትላንታ ከተማ ባደረገው ስብሰባ ላይ ያሳለፈውን ውሳኔ ከራሱ ከቦርዱ ህገ-ደንብና አሰራር ውጭ መሆኑን በማመንና ጉዳዩንም ከህዝብ ፍላጎትና ስሜት አኳያ እንደገና መክሮበት የሰከነ፣ የበሰለና አርቆ አስተዋይነት የታከለበት ህዝባዊ ውሳኔ ሲያሳልፍ ብቻ ነው።

የህዝብን ስሜት ያገናዘበ፣ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን፣ እይታና ፍላጎት ያካተተ ውሳኔ ደግሞ፣ ፌዴሬሽኑን ከተላያዩ አደጋዎች ሊያድኑት እንዲሚችሉ ከማመናችንም በላይ፣ በአትላንታ የሚደረገው 28ኛው የሰሜን አሜሪካ የስፖርትና የባሕል ዝግጅት የተሳካ እንዲሆን፣ የበኩላችንን ድርሻ በብቃት እንደምንወጣ በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እንወዳለን።

ለበለጠ መረጃ፣ በ 404-379-8795 ይደውሉልን።

ከአክብሮት ጋር

በአትላንታ የተለያዩ የሲቪክ ማኅበራት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና፣ አገር ወዳድ ግለሰቦች።